# በቤተ ክህነት ላይ የተጠመደ ፈንጂ

# የወያኔ ፀረ ተዋህዶ ዘመቻ

በቀለ ገብረ ማርያም

አንድን ሀገር ለማፈራረስና ለመናድ የሚነሳ ከፋፋይ ኃይል በቅድሚያ የዚያን ሀገር ሕዝብ ስነ ልቦና ማጥቃትና ሕዝብን የሚያስተሳስሩትን መዋቅሮቹንና ተቋሞቹን ማሽመድመድ፣ ቅርስና ታሪኩን መከለስና ማበላሸት አለበት። የመለስ ወያኔ ኢትዮጵያ የመቶ ዓመት ታሪክ ያለት ሀገር ናት ሲል በ1967 የፖለቲካ መርሀ ግብሩ ባሰፈረው መሰረት የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት የለው ም፡ የርስ በርስ ቅራኔው ዋና ነው፣መለያየት መገንጣጠል አለበት ብሎ ለማሳመን ደግሞ ኢትዮጵ ያዊነትን መናድ ነበረበት። በዚህም መሰረት ሕዝብን በክልልና በብሄረሰብ ሸንሽኖ ኢትዮጵያዊነ ትን ተፃሮ ዘመቻውን አጧጧፈ ። በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ የከፈተውና ዛሬም የቀጠለው ዘመቻ የዚህ ነፀብራቅ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብን የሚያስተሳስሩት የጋራ ታሪክ አለውና ይህን መካድና የሀሰት ወሬ ነው ብሎ ማክቸልቸል የመጀመሪያው ስራ ነበርና/ነውና ወያኔ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀመሮ የራሱንም የዘመዶቹንም ፀረ ታሪክ ዘመቻ ሲያስተጋባ ቆይቷል። መለስ ዜናዊ የኤርትራን በኢትዮጵያ በቅኝ መገዛት ለማሳመን ከ 300 ገፅ በላይ መፅሀፍ መፃፉም የሚታወስ ነው። ትግራይ በአማራው ተበዝብዛ ለድህነት ተዳረገች ብሎ ወያኔ ምልምሎቹን ሲያስተምር ነበር። ከሶማሊያና ኦነግ ጋር ም ሲወዳጅ የነዚህኑ ክፍሎች ቅኝ ተገዝተናል ትረካ ሲያስተጋባ ቆይቷል። ታሪክን መበረዝና መካድ፣አዲሱን ትውልድንም በውሸት መቃኘት ለወያኔ መሰል ሀይሎች በጣም አስፈላጊ ነው። ወጣቱን ትወልድ በአልባሌ ልምዶችና ጠባዮች መተብተብም በትኩረት በወያኔ የሚሰራ ነው። ከጫት እስከ ኮኬይን፣ በአንጎል አዙር ደረጃ በወሲብ  መጠመድ፣ ዝሙት፣ ግለኝነት፣ ለሆድ መሞ ት፣ ህፃናትን ሳይቀር መድፈር ማስደፈርና በአጠቃለይም የሕዝብን የሞራል ህግ መሰባበርና ዋልጌነትን ማስፈን የወያኔ ፖለቲካ አካል ነው። አንጎሉ ላይ ሽ----ት የሚለው አነጋገር በሚገባ የሚገልጠው ነው። አንጎል ሰለባ፣ ህሊናን መግደል፣ ሰብዕናን ማርከስ፣ውርደትን ማቀፍ፣ የመልከስከስ ኑሮን መኖር--ቀጥሎም ሰለ ሀገር ምንም አለመጨነቅ።

የወያኔ መሪዎች ሥልጣን ከያዙ ከምሮ በትኩረት የተያያዙት ዘመቻ የሀይማኖት ተቋሞችን በቁ ጥጥራቸው ማስገባት ነበር። በዚህም መሰረት ለእስልምና ሀይማኖት ተከታዮችም ሆነ ለኦርቶዶክ ስ ክርሰቲያኖች ካድሬዎች ሼክና አቡነ ተብለው ተመደቡላቸው። በአንድ በኩል ለአክራሪ የሳውዲ ዋሀቢስቶች፣ ለሱዳንና ኢራን ፅንፈኛ ሼኮች ሀገሪቷ ክፍት ትሁን ሲባል በሌላ በኩል ደግሞ ለአፍሪካ ጠንቅ ሆነው በታሪክ ለተመዘገቡ የባዕድ ሚስዮናውያንም መንገዱ ተመቻቸ ።

የሕዝብን ድህነት መክፋትና መባባስ በመጠቀም ባለገንዘቦች ህይማኖት ማስቀየርን ተያያዙት።
የወያኔ አፋኝ ሀይሎችም በአንዋር መስጊድና በአደባባይ ኢየሱስ ምዕመናን ጨፈጨፉ። በወያኔ
ገፋፊነት በአርባጉጉ፤ በአሰቦት ወዘተ ክርስቲያኖች ተጨፈጨፉ። በጅማም እንዲሁ። በየአቅጣጫ
ው የሀይማኖት ግጭቶች ተባባሱ። ወያኔም ፈነደቀ ። በአባ ገብረ መድህን ወይም አቡነ ጳውሎስ
አማካኝነት ወያኔ ዋነኛዋን ቤተ ክርሰቲያን ለማውደም ያደረገው ሁሉ በሕዝብ ይታወቃል።
በአሁኑ ወቅት ደግሞ የአባ ገብረ ሥላሴ ገዳይና የወያኔ ካድሬ የሆነው አባ ገብረመድህን ቤተ
ክርሰቲያኗን ሊያዋርድ እየተፍጨረጨረ መሆኑ በግልፅ እየታየ ነው። በሲኖዶ ተከሰተ ተብሎ
በይፋ እየተራገበ ያለው ንትርክ በመሰረቱ በወያኔዎቹ አቡነ ሳሙዔል (አባ ተከስተ ብርሃን ) ና
ጳጳስ ተብዬው አቡነ ጳውሎስ ያለ አለመግባባት መስሎ ቢቀርብም ዋናው ዓላማው ቤተክህነቱንና
ቤተ ክርሰቲያኗን ማዋረድ መሆኑ ግልፅ ነው። አባ ገብረ መድህን  በቅርቡ ለአንዲት ዕቁባቱ ኤስ
ዩቪ የተባለ ውድ መኪና መስጠት ብቻ ሳይሆን ከቦሌው ሚካስል ከሚሰበሰበው ገንዘብ ድርሻዋን
የመደበላት መሆኑ ተጋልጧል። አባ ገብረ መድህን ባለጌና ዋልጌ፤ ጳጳስ ሊሆን ከቶም የማይገባ
ው ወያኔ ሆኑ ጥርጥር የለውም። ወደ ንግዱ ዓለም ዘው ብሎ ከነጋዴዋ ንግስት ማለትም አዜብ
ጎላ ጋር ተጋጨ ከተባለ ጊዜ ጀምሮ ግን ፍዳው ጨምሯል። አባ ገብረ መድህንን በዋልጌነትና
ሙስና፤ የቤተ ክርሰቲያንና የሲኖድን ህግ በመጣስ የሚከሱት ግንባር ቀደም አቡን አቡነ ሳሙዔ
ል ናቸው። የትላንት አባ ተከስተ ብርሃንና የዛሬ አቡነ ሳሙዔል ደግሞ ያልተናነሱ ወያኔና ባለጌ
ለመሆናቸው ከዚህ በፊትም የታወቀ ጉዳይ ነው። በአዲስ አበባ ምዕመናን ላይ የተሾሙትም ለዚ
ሁ ነው። የሁለቱ ወያኔዎች ግጭት ዝንጀሮ ዝንጀሮን ነከስ ሲሆን በግርግሩና እሰጥ አገባው ግን
ቤት ክርስቲያኒቷ ለቅሌት እንድታደረግና ምዕመናንም ተስፋ እንዲቆርጡ  የታቀደ ነው። ችግሩ
ን ፈቺ ተብሎ ቀንደኛው ወያኔ የጋምቤላ ፍጅት አባት አባይ ፀሐዬ መመደቡም በራሱ ተንኮላቸ
ውን ጠቋሚ ነው።

የስንቱ ሀገር ወዳድ ፀሀፊ ድርሰቶች ታፍነው ባለበት ሀገር በሰሞኑ በ 10 ብር የሚሸጥ የ 56 ገፅ
መፅሀፍ ታትሞ ለገበያ ውሏል። አዘጋጁ ራሱን ተከስተ ብርሃን ብሎ ሲጠራ አባ ገብረመድህንን
ደጋፊ መሆኑን አልደበቀም። የመፅሀፉ ርዕስ “ የጳጳሱ ቅሌት”  የሚል ሲሆን ድርሰቱ አቡነ
ሳሙዔልን ለማዋረድ የተፃፈ ነውና  ኤልቤቴል የተባለች ውሽማ እንዳለቻቸው፡  ሌሎች ቅምጦ
ቻቸው (ስምም ይጠቅሳል) ከዚችው ጋር ዱላ እንደገጠሙ፤ “ ይስእመኒ በሲአመተ አፈሁ” እያሉ
ወጣት ሴቶችን እንደሚስሙ፤ በወሲብ ጥም የሚቃጠሉ ሰው መሆናቸው፤የትግራይ ሀገረ ስብከ
ት ጳጳስ አቡነ መረሐ ክርስቶስ “ አባ ተከስተ ብርሃን ጳጳስ ከሚሆን ምንኩስናውን ገፈን ብንድረ
ው ይሻላል”  ብለው እንደነበር፤ አቡነ ሳሙዔል ዲፕሎም ድሻግሪ ሳይኖራቸው አለኝ እንደሚሉ
ና ከሁሉም ደግሞ የባሰው አቡነ ሳሙዔል የለያለቸው ግብረ ሰዶማዊ እንደነበሩና(በዚህ መልክ
ያወቁትን ወጣት እንዳያወራ አሜሪካ እንደላኩት) ፤ ወንድና ሴት የሚያመጡላቸውን ተላላኪዎ
ች የቤት ክህነት ሹመት እንደሰጡ ወዘተ በዝርዝር ቀርቧል። ሲኖዶሱን ለማዋረድ እንዳንል ይህ
ህገ ወጥ ሲኖዶስ ከተዋረደ ጊዜ አልፏል። ነግር ግን ጳጳሰ የተባሉት ሰዎች በዚህ ዓይነት የዘቀጡ
ባለጌዎች ናቸው ከተባለና ሀቅ ሆነ አልሆነ ይህ ዓይነት ዝቅጠት መድረክ አግኝቶ ከተናፈስ

ቤተ ክርስቲያኗ መጎዳቷ አይቀርም፡፡ የጳጳሱ ቅሌት በርካሽ ዋጋ ቀርቦ በሰፊው እየተሸጠ ያለው ም አለ ምክንያት አይደለም፡፡

በባዕድ ሀገር ያለው ህጋዊው ሲኖድ ይህን ቅሌት በተመለከተ በጊዜው መግለጫና ማብራሪያ መስጠት ሲገባው ዝም አይነቀዝምን የመረጠ ይመስላል፡፡ በወያኔ ጳጳሶች መሀል ያለው ንትርክና ዝቅጠት ቤተ ክርስቲያኗን አይመለከትም ብሎ መደምደም ስህተት ነው፡፡ የመለሰ ቡድን በዚህ በዚያ በንትርኩ ዘው ብሎ ገብቶ ይበልጥ እያተራመሰና በተለይም ቤተ ክርስቲያኗ ኪሳራ እንዲደርስባት እየጣረ ነው፡፡ ይህን ማጋለጥና የወያኔን ተንኮል ማክሸፍ ያስፈልጋል፡፡ በነገራችን ላይ አቡነ ሳሙኤል በመፅሀፉ ውስጥ የተከሰሱሰበት አንዱ “ ጥፋት” በኢንተርኔት ማስቀደስና በ ኢ ሜይል ንስሐ መግባት ይቻላል ይላሉ በሚል ነው፡፡ አይ ኖውና ሶሪ ፐሊስ የሚቀናው አባ ገብረመድህን ከኔ በላይ ስልጡን መጣ ብሎ ይሆን ሰውየውን የጠመዳቸው? ሞኝ ውህ ሲወስደ ው ይስቃል አንዳይሆንብን ብለን እንጂ በሳቅን ነበር!!